የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፵
አዲስ አበባ መስከረም ፳፭ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

29th Year No.40
ADDIS ABABA 6th October, 2023

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺፬/፪ሺ፲፭

ስለራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ………………………………………….ገጽ ፲፭ሺ፩፻፲፯

## Content

Proclamation No. 1294/2023

A Proclamation to provide for Autonomy of Universities ………………………….…… Page 15117

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺፬/፪ሺ፲፭

### የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ አዋጅ

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ነፃ ሆነው እንዲሰሩ ማድረግና በሁሉም ሥራዎቻቸው ላይ በራሳቸው እንዲወስኑ ማድረግ ለተቋማቱ ውጤታማነትና ብቃት መሻሻል፣ ለአገር እድገት፣ ብቃት ያለው የሰለጠነ የሰው ሀብት ለማፍራት፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነትን ለመገንባት ያላቸውን ትልቅ አስተዋፅኦ በመረዳት፤

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ፣ ጥልቅ በሆነ የመማር-ማስተማር እና የምርምር ሥራ የዳበረ ዕውቀት የሚገኝባቸው፣ የፈጠራ ሀሳብና ሥራ የሚስፋፋባቸው፣ በማኅበረሰብ ጉድኝት ለሕብረተሰቡ ተገቢውን የጤናና ሌሎች አገልግሎቶች ጥራቱን ጠብቆ በሰፊው የሚሰጥባቸው ይሆኑ ዘንድ፣ ለሰው ልጆች ዕድገትና ልማት የተሰለፉና ሥራቸውንም በሙሉ ነፃነት የሚያከናውኑ ተመራማሪዎችን፣ መምህራንን፣ ሠራተኞችንና ተማሪዎችን ያቀፉ ተቋማት አድርጎ እንደገና ማደራጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የራሳቸውን የገቢ ምንጮች በማስፋፋት፣ ገቢያቸውን እንዲያሳድጉ በማድረግ ሀገራዊ የልማት ትልሞችን ለማሳካት እንደሚያስችል በመታመኑ፤

### PROCLAMATION NO. 1294/2023

### UNIVERSITY AUTONOMY PROCLAMATION

**RECOGNIZING,** the major role that ensuring operational freedom and self-governance in institutions of Higher Education in enhancing their effectiveness and competence, the country's development, production of competent trained human resource, and the advancement of their international competitiveness plays;

**WHEREAS,** it has become necessary to reestablish Higher Education Institutions that are competitive internationally and that are places where knowledge is acquired through profound teaching-learning and research; innovative ideas and works flourish; quality and appropriate health and other services are provided extensively to communities via community engagement; where faculty, researchers, employees, and students are committed to human growth and development and who carry out their works with full freedom;

**WHEREAS,** it is believed that letting institutions of Higher Education expand the sources of their revenues and thereby increase their revenues would enable achieve national development goals;

ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከላይ የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ለማሳካት እንዲያስችላቸው፣ ለተሻለ የአካዳሚያዊ፣ የፋይናንስና የአስተዳደር ነፃነቶች የራስ-ገዝ እንዲሆኑ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ እና አዲስ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ሊቋቋም የሚችልበትን ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ስለራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፺፬/፪ሺ፲፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውሰጥ፡-

፩/ **"ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር"** ማለት እንደቅደም ተከትሉ የትምህርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፪/ "**ቦርድ**" ማለት የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው የሥራ አመራር ቦርድ ነው፤

፫/ **"ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ"** ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የፋይናንስ፣ተቋማዊ ፣አስተዳዳራዊ እና አካዳሚያዊ ነፃነት ኖሮት በሕግ የተቋቋመ፣ የትርፍ ዓላማ የሌለው እና የዜጎችን ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በመንግሥት በጀት ድጋፍ የሚደረግለት የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው፤

፬/ **"ተቋማዊ ነፃነት"** ማለት ተቋማት የራሳቸውን ከፍተኛ አመራር የመምረጥ፣ የተቋማትን መዋቅርና ቅርፅ በነፃነት የመወሰንና የመተግበር፣ በውስጣቸው ሕጋዊ አካላት የመፍጠር፣ እንዲሁም አማራጭ የአስተዳደር አካላትን በነፃነት የመሾም እና የማንሳት ነፃነት፣ በተጨማሪም የውስጥ አሰራር መመሪያና ማንዋል የማውጣት እና ኢንተርፕራይዞችን የማቋቋምና የመጠቀም ነፃነትን ያጠቃልላል፤

**WHEREAS,** it has become necessary to grant autonomy to institutions of higher education to enable them attain the objectives stated above and to put in place systems for a better academic, financial and administrative freedom to existing institutions of higher education and to design mechanisms for the establishment of new ones;

**NOW THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "A Proclamation to provide for Autonomy of Universities" Proclamation No. 1294/2023.

### 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ "**Ministryor Minister**" means the Ministry or Minister of Education respectively;

2/ **"Board"** means the management board of an autonomous university;

3/ **"Autonomous University"** means a public higher education institution established by law in accordance with this Proclamation, having financial, administrative and academic autonomy with no gain objectives and with government budgetary support with the view to ensure citizens' equitable access;

4/ **"Institutional Autonomy"** shall include the autonomy of institutions to elect their own leaders, to freely determine and implement the form and structure of their institutions, to establish internal organs, to freely appoint and remove alternative administrative organs, formulate internal guidelines and manuals as well as to establish and make use of enterprises;

፭/ **"አካዳሚያዊ ነፃነት"** ማለት የአካዳሚክ ሠራተኞችና ተማሪዎች፣ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲውና የትምህርት ክፍሎች የመማር-ማስተማር፣ የምርምርና የማኅበረሰብ ጉድኝት ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ ከማንኛውም መንግስታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና አስተዳደራዊ ተፅዕኖና ጣልቃ ገብነት ነፃ ሆነው መሥራት መቻል ነው፤

፮/ **"አስተዳደራዊ ነፃነት"** ማለት አንድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የራሱን አሰተዳደራዊ፤ አካዳሚያዊ፤ የፋይናንስ አስተዳደር እና የሰው ሀብት አስተዳደር ጉዳዮችን እንዲሁም የአሰራር ሥርዓቶችን በተመለከተ ውጤታማ የውሳኔ አሰጣጥ ዘዴን በመቀየስ ተቋማትን የማስተዳደር ነፃነት እና ተጠያቂነት ነው፤

፯/ **"የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ማኅበረሰብ"** ማለት የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ተማሪዎችና ሠራተኞች ማለት ነው፤

፰/ **"ሠራተኛ"** ማለት የራስ-ገዝ ዩኒቨርሲቲ አካዳሚክ፣ አስተዳደር፣ አካዳሚክ ቴክኒክ ረዳትና ክሊኒካል ሠራተኛ ማለት ነው፤

፱/ **"የሠራተኛ አስተዳደር"** ማለት የአካዳሚክ፣ የአካዳሚክ ቴክኒክ ረዳት፣ የክሊኒካልና የአስተዳደር ሠራተኞች ቅጥር፣ ዝውውር፣ የደረጃ ዕድገት፣ ስንብት ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም እና ሌሎች ተያያዥ ተግባራት አስተዳደራዊ ሥርዓት ነው፤

፲/ **"የአካዳሚያዊ ማኅበረሰብ"** ማለት ሁሉም የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ተማሪዎችና የአካዳሚክ ሠራተኞች ማለት ነው፤

፲፩/ **"የአካዳሚያዊ ኃላፊ"** ማለት በራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው የውስጥ መመሪያ መሠረት የተሰየመ የአካዳሚክ ሥራ መሪ ማለት ሲሆን የዩኒቨርሲቲውን ሬጂስትራር እና ላይብረሪያን ይጨምራል፤

፲፪/ **"የአካዳሚያዊ ሠራተኛ"** ማለት በማስተማር፣ በምርምር እና በማኅበረሰብ ጉድኝት የተሰማራ የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ሠራተኛ ማለት ነው፤

፲፫/ **"የአካዳሚክ ቴክኒካል ረዳት»** ማለት ለመማር ማስተማር፣ ለምርምርና ለማህበረሰብ ጉድኝት ሥራ ሂደት ሙያዊ እገዛ እንዲሰጥ ሆኖ የተቀጠረ፤ ነገር ግን የአካዳሚም ሆነ የአስተዳደር ሠራተኛ ያልሆነ ሠራተኛ ማለት ነው፤

5/ **"Academic Freedom"** means the freedom of academic staff, students, the autonomous university and academic units under it to discharge their duties in teaching/ learning, research and community engagement, and being free from any governmental, political, social or administrative influence and/or intervention;

6/ **"Administrative Autonomy"** means the freedom and accountability of a higher learning institution in putting in place its own administrative, academic, financial and human resource management systems and effective decision making mechanisms to manage the institution;

7/ **"Autonomous University Community"** means the staff and students of an autonomous university;

8/ **"Employee"** means the academic, administrative, academic technical assistant, and clinical staff of an autonomous university;

9/ **"Staff Administration"** means a system of the administration of the affairs relating to the employment, transfer, promotion, dismissal, salaries and benefits and other related matters of academic, academic technical assistants, clinical and administrative staff;

10 **"Academic Community"** means all students and academic staff of an autonomous university;

11/ **"Academic Officer"** means a leader appointed pursuant to internal rules of an autonomous university to lead academic affairs and shall include university registrars and librarians;

12/ **"Academic Staff"** means a staff of an autonomous university involved in teaching, research and community engagement;

13/ **"Academic Technical Assistant"** means a staff that is neither academic nor administrative and is employed to render professional assistance in teaching learning, research and community engagement;

፲፬/ **"የአስተዳደር ሠራተኛ"** ማለት ከአካዳሚያዊ፣ ከአካዳሚክ ቴክኒክና ክሊኒካል ሠራተኛ ውጭ የተቀጠረ የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ሠራተኛ ማለት ነው፤

፲፭/ **"የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ"** ማለት የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፶፪/፪ሺ፲፩ ነው፤

፲፮/ **"ዩኒቨርሲቲ"** ማለት በከፍተኛ ትምህርት አዋጁ መሰረት ዩኒቨርሲቲ ሆኖ የተቋቋመ የመንግስት ከፍትኛ የትምህርት ተቋም ነው፤

፲፯/ **"የማስተማሪያ ሆስፒታል"** ማለት ባለቤትነቱ የከፍተኛ ትምርት ተቋም የሆነ የጤና አገልግሎትን ከመማር ማስተማር እና ምርምር ጋር አጣምሮ የሚሰጥ ሆስፒታል ማለት ነው፤

፲፰/ **"ኮሌጅ"** ማለት በሥሩ የትምህርት ክፍሎችን፤ ትምህርት ቤቶችን፤ ማዕከላትንና ሌሎችንም አሀዶች የያዘ መማር ማስተማር፣ የምርምርና የማኅበረሰብ ጉድኝት የሚሰራ የዩኒቨርሲቲው አካል ማለት ነው፤

፲፱/ **"ኢንስቲትዩት"** ማለት ራሱን ችሎ ወይም በኮሌጅ ውስጥ ሆኖ የመማር ማስተማር፣ የምርምርና የማኅበረሰብ ጉድኝት ለማካሄድ የተለየ ተልዕኮ ተሰጥቶት የሚሰራ አሀድ ነው፤

፳/ **"የአካዳማያዊ አሃድ"** ማለት ዲግሪዎች፤ የድህረ ምረቃ ዲፕሎማዎችና የልዩ ሥልጠና የምሥክር ወረቀቶች የሚያስገኙ ትምህርቶች የሚሰጡበት የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው አካል ሲሆን ትምህርት ቤቶችን፤ ትምህርት ክፍሎችን፣ ማዕከላትንና ሌሎችንም ተመሳሳይ መርሃ-ግብር ያላቸውን የአካዳሚ አሀዶችን ይጨምራል፤

፳፩/ **"የትምህርት ክፍል"** ማለት የአንድ ተቋም አካል የሆነ ኮሌጅ፣ ፋኩልቲ፤ትምህርት ቤት፣ ኢንስቲትዩት፣ ማዕከል ወይም ዲፓርትሜንት ነው፤

፳፪/ **"ማኅበረሰባዊ ጉድኝት"** ማለት ሙያዊ አገልግሎቶችን ለማበርከት፣ በጋራ ችግሮችን ለመፍታት የሚደረጉ የምክክር መድረኮችን ለማመቻቸት፣እንዲሁም የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ልውውጥ ለማድረግ ሲባል በራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲውና ከዩኒቨርሲቲው ውጭ ባለው ማህበረሰብ መካከል የሚደረግ ጉድኝት ነው፤

፳፫/ **"የሂሳብ ዓመት"** ማለት የኢትየጵያ መንግስት የበጀት ዓመት ነው፤

14/ **"Administrative Staff"** means a staff of an autonomous university that is employed neither as academic, nor academic technical assistant, nor clinical;

15/ "**Higher Education Proclamation**"means Higher Education Proclamation No. 1152/2011;

16/ **"University"** means a public higher education institution established pursuant to the Higher Education Proclamation;

17/ "**Teaching Hospital**" means a hospital rendering health services in conjunction with teaching learning and research and owned by a higher learning institution;

18/ **"College"** means an organ of a university engaged in teaching/ learning, research and community engagement and having under it academic departments, schools, centers and other units;

19/ **"Institute"** means an independent organ or a unit under a college given a special mission and is engaged in teaching/ learning, research and community engagement;

20/ **"Academic Unit"** means an organ of an autonomous university wherein education that result in the awarding of degrees, post-graduate diplomas, certificates for special trainings are offered and shall include schools, educational units, centers and other units having similar programs;

21/ "**Educational Unit**" means a college, faculty, school, institute, center or department which is part of an institution;

22/ "**Community engagement"** means an engagement established between an autonomous university and a community outside of the university for the purposes of rendering professional services, arrangement of dialogue fora to jointly solve problems and exchange of knowledge and technology;

23/ " **Fiscal Year**" means a budget year of the Ethiopian Government;

፳፬/ **"የውስጥ ገቢ"** ማለት ከመንግስት መደበኛና ካፒታል በጀት ውጭ የሚገኝ ማንኛውም ዓይነት ገቢ ማለት ነው፤

፳፭/ **"ልዩ ፍላጎት"** ማለት ሥርዓተ ትምህርትን፣ የተግባቦት መንገዶች ወይም የመማር ማስተማር አካባቢን በማስማማት የትምህርት ጥቅሞችን ግለሰባዊ ልዩነቶችን መሠረት በማድረግ አገልግሎት የሚሰጥ የትምህርት ዓይነት ነው፡፡ ይህም ማንኛውንም በልዩ ትምህርት ቤቶች፣ በልዩ ክፍሎች እና በአካቶ ትምህርት የሚሰጥ የትምህርት አግልግሎቶችና ድጋፎችን የሚያጠቃልል ነው፤

፳፮/ በዚህ አዋጅ በወንድ ፆታ የተመለከተ አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በራስ ገዝ የኒቨርሲቲ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ፬. ስለመቋቋም

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይቋቋማል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቋቋም ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ በከፍተኛ ትምህርት አዋጁ መሠረት የተቋቋመ የመንግስት ዩኒቨርሲቲ ወይም አዲስ ዩኒቨርሲቲ ሊሆን ይችላል።

## ፭. የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ መስፈርቶች

ራስ-ገዝ ዩኒቨርሲቲ ለማቋቋም የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት ያለባቸው ሲሆን ዝርዝሩ በዚህ አዋጅ መሠረት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡-

፩/ ጠንካራ የፋይናንስ አቅም፤

፪/ በጥናትና ምርምር ለማህበረሰብ ተኮር ተግባራት የሚኖረው ፋይዳ፤

፫/ አካዳሚያዊ ተወዳዳሪነት፤

፬/ ለሀገር ልማትና እድገት የሚኖረው ፋይዳ፤

24/ "**Internal Revenue**" means any revenue earned outside of government regular and capital budget;

25/ **"Special Needs"** means a kind of education that is offered through adaptation of curricula, means of communication, noting the usefulness of education, taking individual differences into consideration and shall include education offered in special schools, special units, inclusive education and support;

26/ In this Proclamation, expressions in the masculine gender shall include the feminine gender.

## 3. Scope of Application

This Proclamation shall be applicable to autonomous universities.

## 4. Establishment

1/ When deemed necessary, an autonomous university may be established by a Regulation of the Council of Ministers in accordance with this Proclamation.

2/ An Autonomous University to be established pursuant to Sub-Article (1) of this Article may either be a public university established in accordance with the Higher Education Proclamation, or a new one.

## 5. Criteria for Establishing an Autonomous University

Subject to details to be formulated in the Directive to be issued by the Ministry, the following criteria shall have to be fulfilled in establishing an Autonomous University:

1/ A strong financial capacity;

2/ Usefulness in community focused research activities;

3/ Academic competitiveness;

4/ Usefulness in national development and advancement;

፭/ በነፃነትና በተጠያቂነት ትምህርትና ምርምርን በብቃት ለማካሄድ የዘረጋው ሥርዓት፤

፮/ ሌሎች ሚኒስቴሩ የሚወስናቸው መስፈርቶች፡፡

**፮. ዓላማዎች**

አዋጁ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ ዕውቀትን በማስፋፋት፣ በመማር ማስተማር፣ በጥናትና ምርምር፣ በቴክኖሎጂ ፈጠራና ሽግግር፣ የማኅበረሰብ ጉድኝት በማድረግ፣ ማህበራዊ፤ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ዕድገትን ማሳለጥና ማስፋፋት የሚችሉ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲዎችን ማቋቋም፤

፪/ የአካዳሚና የኢንዱስትሪ ትሥሥርን ማጠናከር የሚችሉ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲዎች የሚቋቋሙበትን ሥርዓት መፍጠር ፣ በገቢ ራሳቸዉን የሚችሉበት ቁመና እንዲኖራቸው ገቢ የማመንጨት፣ በውጤታማነትና ወጪ ቆጣቢነት የሚያስተዳድሩበት ሥርዓት መገንባት፡፡

**፯. የራስ- ገዝ ዩኒቨርሲቲ መሪ እሴቶች**

፩/ እውነትን የመሻትና የመግለፅ ነፃነት፡፡

፪/ አመክኖዓዊነትና ተቀባይነት ባለው የሀሳብ ልውውጥ መርህ ላይ የተመሠረተ ሀሳብን የመግለፅ ነፃነት፡፡

፫/ አካዳሚያዊ ተወዳዳሪነትና በትብብር ላይ የተመሰረተ ዝምድና፡፡

፬/ በተልዕኮ እሴት ላይ የተመሠረተ ታዋቂነት፡፡

፭/ ተቋማዊ ነፃነትን ከተጠያቂነት ጋር ማረጋገጥ፡፡

፮/ ሙስናን የመታገል ባህል፡፡

፯/ ፍትህ ፍትሃዊነትንና የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ፡፡

፰/ ሀብትን በቁጠባ የመጠቀምና ንብረትን መከባከብ፡፡

፱/ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት፡፡

5/ The System established by the institution to ably, autonomously and accountably carry out education and research; and

6/ Other criteria to be set by the Ministry.

**6. Objectives**

The Proclamation shall have the following as its objectives:

1/ To establish Autonomous Universities that shall facilitate social, political, Economical and cultural development through the expansion of knowledge, teaching and learning, research, innovation and technology transfer and community engagement;

2/ To create a system for the establishment of autonomous universities that are able and competent to strengthen linkages between the academia and industry with the view to enable them have good standing to generate revenues and thereby builed a system to become self-sufficient by efficiently and judiciously managing their revenues.

**7. Guiding Principles of Autonomous Universities**

1/ Freedom to seek truth and reveal same.

2/ Reasoning and the freedom of expression based on reasoning and free exchange of ideas.

3/ Academic competitiveness and relations based on cooperation.

4/ Famousness based on values of mission;

5/ Ensuring institutional autonomy with accountability.

6/ Culture of resisting corruption.

7/ Ensuring justice and rule of law.

8/ Austere use of assets and caring for property.

9/ Rendering efficient and quality services.

፲/ የቁልፍ ባለድርሻዎች ተሳትፎና ውክልና ማረጋገጥ፡፡

፲፩/ ዲሞክራሲያዊ ባህልን እና ሥነ-ምግባርን በማሳደግ የባህል ብዝሃነትን መጠበቅ፡፡

፲፪/ ለምስጉን ሰው እውቅና መስጠት፡፡

## ፰. የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ተግባርና ኃላፊነት

የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች አሉት፡-

፩/ ትምህርትና ስልጠና፣ ጥናትና ምርምር፣ የማህበራዊ ጉድኝት ሥራዎችን ማከናወን፤ የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎችና መሪ እሴቶችን የሚያከብር የትምህርትና ምርምር ተቋም መሆኑን ማረጋገጥ፤

፪/ በአገሪቱ ፍላጎትና በልማት ትኩረት ሴክተሮች ላይ በመመስረት የትምህርት ፕሮግራሞችን የመቅረፅ፣ የከፍተኛ ትምህርትን የመስጠት፣ በእውቀት፣ በክህሎት እና በአመለካከት የታነፁ ምሩቃንን የማፍራት እና የተለያዩ የትምህርት ማስረጃዎችን የመስጠት፤

፫/ እንደ አግባብነቱ በማስተማሪያ ሆስፒታሎች የጤና አገልግሎት መስጠት፤

፬/ መዋቅሩን እንዳስፈላጊነቱ እንደገና ማደራጀት፤

፭/ የአካዳሚ አሀዶችን መመሥረት፤ ማዋሀድና ማፍረስ፤

፮/ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚያወጡት መስፈርት መሠረት ተማሪዎችን መቀበል፤

፯/ የአዎንታዊ እርምጃ ፖሊሲ መቅረፅና ተግባራዊ ማድረግ፤

፰/ ለየት ያለ ተሰጥዖና የላቀ ውጤት ላላቸው ተማሪዎች ነፃ የትምህርት ዕድል መስጠት፤

፱/ አገራዊና ዓለም አቀፍ ተሞክሮ የሠራተኛ መብቶችን ስታንዳርድ እና አሰራርን መነሻ በማድረግ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ሠራተኞችን መቅጠር፣ ማስተዳደር፣ ማሰናበት፣

፲/ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣው መመሪያ መሠረት የግዢ፣ የንብረት አስተዳደር እና የፋይናንስ ሥርዓት መዘርጋት፤

10/ Ensuring the participation and representation of key stakeholders.

11/ Preserving cultural multiplicity through democratic culture and the development of ethics.

12/ Acknowledging deserving citizens.

## 8. Duties and Responsibilities of an Autonomous University

An Autonomous University shall have the following duties and responsibilities:

1/ Educate and train, conduct research and perform community engagements; ensure that it is an educational and research institution that respects the objectives and principles of higher education;

2/ On the basis of national demands and focusing on priority sectors, design educational programs, offer higher education trainings, produce skilful graduates equipped with good outlooks, and issue various educational testimonials;

3/ Render health services as appropriate in teaching hospitals;

4/ Reorganize its organizational structure when desired;

5/ Establish, merge and dissolve academic units;

6/ Admit students on the basis of the criteria to be set pursuant to this Proclamation;

7/ Design and implement a policy on affirmative action;

8/ Offer scholarships to students with special talents and exceptional performances;

9/ Employ, administer, and dismiss employees on the basis of national and international standards on labor rights and the Directives to be issued by the Board;

10/ Establish systems for procurement, property administration and finance pursuant to the Directive to be issued in line with this Proclamation;

፲፩/ አካዳሚያዊ መጽሔቶችን፣ የዜና መጽሔቶች እና የመጽሐፍት ማዕከላትን ማቋቋም፤

፲፪/ መንግሥታዊም ሆኑ መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ትብብር መፍጠር፤

፲፫/ የስፖርት፣ መዝናኛና ሥነ-ጥበብ ማዕከላትን ማቋቋምና ማጎልበት፤

፲፬/ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት የሚያስችለውን የገቢ ማስገኛ ሥራዎች በዚህ አዋጅ እና አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት መስራት፣ ገቢውን ለተቋቋመለት ዓላማ ማዋል፤

፲፭/ ለሚሰጠው አገልግሎት በቦርድ በሚወጣ መመሪያ መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ማስከፈል፣ ገቢውን ማስተዳደር እና ለተቋቋመለት ዓላማ ማዋል፤

፲፮/ የስራ ዕቅድ እና በጀት ማዘጋጀት እና በቦርዱ ሲፀድቅ ተግባራዊ ማድረግ፤

፲፯/ ከመንግሥት የሚያገኘውን ማንኛውንም ድጋፍ ለተደረገለት ዓላማ ማዋል፣

፲፰/ ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ ወይም ለህብረተሰቡ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላበረከቱ ግለሰቦች እውቅና፣ ሽልማት ወይም የክብር ዲግሪ መስጠት፤

፲፱/ የተማሪዎች የሥነ-ምግባር ደንብ ማውጣት፣ የዲሲፕሊን እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት፤

፳/ የተቋቋመበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉትን ሌሎች አስፈላጊ ተግባሮች ማከናወን፡፡

## ክፍል ሁለት
## መዋቅራዊ አደረጃጀትና አስተዳደር

### ፱. የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ አደረጃጀት

ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡-

፩/ ቻንስለር፤

፪/ የሥራ አመራር ቦርድ፤

11/ Establish academic journals, academic newsletters and book centers;

12/ Forge cooperative relationships with governmental and non-governmental institutions;

13/ Establish and develop sports, recreational and cultural centers;

14/ In accordance with this Proclamation and other relevant laws, perform income generating activities enabling it fulfil the objectives for which it is established and make use of such income to further its objectives;

15/ In line with the Directive to be issued by the Board, levy charges for the services it renders, administer its revenues and make use of the revenues it generates to achieve the objectives for which it is established;

16/ Formulate its work plan and budget and implement same when approved by the Board;

17/ Make use of any governmental support for the purpose for which it is made;

18/ Give recognition and awards to or bestow honorary degrees to individuals with high achievements, or those that have made high social contributions;

19/ Issue codes of conduct for students and design a system that enables taking disciplinary measures; and

20/ Perform other activities that enable it fulfil the objectives for which it is established.

## PART TWO
## ORGANIZATIONAL STRUCTURE AND GOVERNANCE

### 9. Structure of the Autonomous University

An Autonomous University has the following organs:

1/ Chancellor;

2/ Board of Governance;

፫/ ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንቶች፤

፬/ ሴኔት፤

፭/ የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ካውንስል፣ የማኔጅንግ ካውንስልና ኤግዚክዩቲቭ ኮሚቴ፤

፮/ ተጠሪነታቸው ለቦርድ የሆኑ የጥራት ማረጋገጫ ክፍል እና የውስጥ ኦዲት ክፍል፤

፯/ ራስ-ገዝ ዩኒቨርሲቲ የተቋቋመበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ እንደአስፈላጊነቱ የሚያደራጃቸው ሌሎች ክፍሎች፡፡

**፲. ቻንስለር**

፩/ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው በውስጥ አስተዳደሩ ውስጥ ሳይገባ፣ በአገር ውስጥም ሆነ በዓለም-አቀፍ ደረጃ የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲውን ሥራና መልካም ስም የሚያጎላ፣ እንደ ከፍተኛ አምባሳደርና የበላይ ጠባቂ የሚያገለግል፣ ሀብት የሚያፈላልግ እና ሌሎች ለዩኒቨርሲቲው በጎ ተግባራትን የሚያከናውን ቻንስለር ይኖረዋል።

፪/ የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ቻንስለር በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾም ሲሆን የሥራ ዘመኑ አምስት ዓመት ይሆናል።

**፲፩. የሥራ አመራር ቦርድ**

፩/ የቦርዱ አባላት ከመንግሥት ጋር በመመካከር በሚኒስትሩ ይሰየማሉ፡፡

፪/ ቦርዱ በዋናነት ብቃት ላይ ተመሥርቶ፤ በተቻለ መጠን የፆታ፣ የብዝሃነትን እና የባለድርሻ አካላትን ስብጥር የጠበቀ ሆኖ ከዘጠኝ (፱) እስከ አስራ አንድ (፲፩) አባላት ይኖሩታል፡፡ የተቋሙ ፕሬዚዳንት ድምፅ የማይሰጥ የቦርዱ አባልና ጸኃፊ ይሆናል፡፡

፫/ የቦርድ አባላት የሥራ ዘመን አራት ዓመት ሆኖ የቦርዱ ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡

፬/ የቦርድ አባላት ከሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመን በላይ ለቦርድ አባልነት ሊመረጡ አይችሉም፡፡

፭/ የቦርድ አባላት ጥቅማጥቅም እና ተመሳሳይ ጉዳዮች በዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት አቅራቢነት በቻንስለሩ ይወሰናል፡፡

3/ President and Vice Presidents;

4/ Senate;

5/ Autonomous University Council, Managing Council, and Executive Committee;

6/ Quality Assurance Section and Internal Audit Section accountable to the Board; and

7/ Other sections to be organized by the Autonomous University as necessary.

**10. Chancellor**

1/ An Autonomous University shall have a Chancellor who, without entering into University internal governance, will symbolize the work and good will of the University nationally and internationally, serve as a senior ambassador, search for funds and resources, and undertake other good will activities.

2/ The Chancellor shall be appointed by the Prime Minister and shall serve for the duration of five years.

**11. Board of Governance**

1/ The Minister shall, in consultation with the Government, appoint Memebers of the Board.

2/ With due regard to gender, diversity and other stakeholders' representation, based on efficiency the Board shall have nine (9) to eleven (11) members. The President shall be a non-voting member and secretary of the Board. .

3/ The term of service for members of the Board shall be four years except the Chairperson and the Vice Chairperson, whose term shall be five years.

4/ Members of the Board may not be elected for more than two consecutive terms.

5/ Benefits and related matters to members of the Board shall be decided by the Chancellor up on proposal by the President of the Autonomous University.

## ፲፪. ከቦርድ አባልነት ስለመነሳት

የቦርድ አባልነት በሚከተሉት ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል፡-

፩/ የአገልግሎት ዘመን ሲያበቃ፤
፪/ በፈቃደኝነት በመልቀቅ፤
፫/ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ፤
፬/ በሞት ወይም በህመም ምክንያት፤
፭/ በከባድ የዲስፐሊን ጥፋት፣ በችሎታ ማጣት ወይም በስብሰባዎች ላይ ያለፈቃድ በተከታታይ ለሶስት ጊዜያት ያለመገኘት።

## ፲፫. የቦርዱ ተግባርና ኃላፊነቶች

ቦርዱ የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ የአመራር አካል ሲሆን የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩/ በዚህ አዋጅ ለራሰ ገዝ ዩኒቨርሲቲው የተሰጡ ተግባር እና ኃላፊነቶች ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

፪/ የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲውን የውስጥ መዋቅርና አደረጃጀት ያፀድቃል፤

፫/ የራስ ገዝ ዩኒቨርስቲውን የሰው ሀብት አስተዳደር፣ የፋይናንስ አስተዳደር፣ የግዥና ንብረት አስተዳደር መመሪያዎችንና አሰራር ሥርዓት ያወጣል፣ በተጠያቂነት ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤

፬/ የራሱን የውስጠ ደንብ እና መመሪያዎችን መርምሮ ያፀድቃል፤

፭/ ይህን አዋጅ ተከትሎ ተጠንቶ የሚቀርብለትን የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲውን ሠራተኞች ደሞዝ፣ አበል እና ጥቅማጥቅም እንደ ዩኒቨርሲቲው የመክፈል አቅምና የሥራ አፈፃፀም ታሳቢ በማድረግ መርምሮ ያፀድቃል፤

፮/ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ መሠረት ፕሬዚዳንቱን አወዳድሮ ሶስት እጩዎችን ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለቻንስለሩ አቅርቦ ያሾማል፤

## 12. Termination of Membership of the Board

The following may be grounds for termination from Board Membership:

1/ Due to expiry of term of service;
2/ Due to resignation;
3/ Due to conviction for serious crime;
4/ Due to death or illness;
5/ Due to grave disciplinary breaches, loss of capacity, or absence from meetings for three consecutive times without good cause.

## 13. Powers and Responsibilities of the Board

The Board shall be the highest governance body of the Autonomous University and shall have the following powers and responsibilities:

1/ Ensure the implementation of powers and responsibilities of the Autonomous University granted under this Proclamation;

2/ Examine and approve the internal structure and organization;

3/ Adopt Directives pertaining to Human Resource Management; Financial Administration; Procurement and Property Administration and ensure their implementation with accountability;

4/ Draw up its internal rules and procedures;

5/ Examine and approve salary, allowances and other benefits of employees of the Autonomous University in accordance with this Proclamation; and based on performance and the University's capacity to pay;

6/ In accordance with Directives to be issued under this Proclamation, facilitate the selection of the President and recommend three presidential candidates for appointement by the Chancellor;

፯/ ምክትል ፕሬዚዳንቶችን በብቃት ላይ በተመሠረተ ውድድር ሥርዓት ተለይተው ሲቀርቡለት ፕሬዚዳንቱን በማማከር ይሾማል፤

፰/ የፕሬዚዳንቱንና ምክትል ፕሬዚዳንቶችን ደመወዝ፣ አበልና ጥቅማጥቅም ይወስናል፤

፱/ ፕሬዚዳንቱ ኃላፊነትን ከመወጣት አኳያ ከፍተኛ የሆነ ድክመት ካሳየም ሆነ በሌላ የዲሲፕሊን ምክንያት ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ መሠረት ከኃላፊነት እንዲነሳ ለቻንስለሩ ያቀርባል፤

፲/ ምክትል ፕሬዚዳንቶችን ኃላፊነትን ከመወጣት አኳያ ከፍተኛ የሆነ ድክመት ካሳዩም ሆነ በሌላ የዲሲፕሊን ምክንያት ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ መሠረት ከኃላፊነት ማንሳትን ጨምሮ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወስዳል፤

፲፩/ የዩኒቨርሲቲውን ዓመታዊ ዕቅድና በጀት መርምሮ ያፀድቃል፤

፲፪/ የራስ-ገዝ ዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት በየወቅቱ የሚያቀርበውን የአፈፃፀም ሪፖርት መርምሮ ያፀድቃል፤

፲፫/ የፕሮፌሰርነት ማዕረግ በሴኔት ሲቀርብለት መርምሮ ያፀድቃል፤

፲፬/ በሕግ አግባብ ሥልጣን የተሰጠው የውጭ ኦዲተር የራስ ገዝ ዩኒቨርስቲውን የክዋኔና ሌሎች ኦዲት እንዲያደርግ ይወስናል፤ የኦዲት ግኝቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃዎች መወሰዳቸውን ይከታተላል፤

፲፭/ ለዩኒቨርሲቲው የሚከፈሉ የትምህርትና ሌሎች የአገልግሎት ክፍያዎችን የተጠቃሚዎችን የመክፈል አቅም ያገናዘበ መሆኑን በማረጋገጥ በመመሪያ ይወስናል፤

፲፮/ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የሚመሠረቱ፣ የሚዋሀዱ፣ የሚከፋፈሉ፣ የሚለወጡ ወይም የሚፈርሱ ሕጋዊ ሰውነት ያላቸውን የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ድርጅቶችን ይወስናል፤

፲፯/ የጥራት ቁጥጥር እና የውስጥ ኦዲት ሪፖርቶችን ይመረምራል፣ ያፀድቃል፤የእርምት እርምጃዎችን ይከታተላል፤

7/ In consultation with the President, appoint vice presidents submitted to it through competitive process;

8/ Determine salary and other benefit packages to the President and his deputies;

9/ Propose the removal of the President by the Chancellor whenever the President manifests serious incompetence or commits other disciplinary violations in connection with discharge of responsibilities, based on the Directives to be issued under this Proclamation;

10/ Take disciplinary measure including removal, whenever the Vice Presidents manifest serious incompetence or commits other disciplinary violations in connection with discharge of responsibilities, based on the Directives to be issued under this Proclamation;

11/ Examine and approve annual plan and budget of the Autonomous University;

12/ Examine and approve performance reports to be submitted by the President from time to time;

13/ Examine and approve the rank of Professorship submitted to it by the Senate;

14/ Entrust the legally authorized External Auditor to audit performance and other activities of the Autonomus University; and monitor the taking of corrective measures on the audit findings;

15/ Taking into account the purchasing power of the service recipients, fix tuition and other service charges to be levied by the Univisrity through a Directive;

16/ Determine Organs of the Autonomous University that might be established, merged, divided, changed, or dissolved in accordance with the relevant laws;

17/ Examine and approve quality control and internal audit reports and follow-up their corrective measure implementation;

፲፰/ ከፍርድ ቤት ውጪ የሚደረግ የግልግል ዳኝነትን ይፈቅዳል፣ ይወስናል፣ መርምሮ ያፀድቃል፤

፲፱/ የራስገዝ ዩኒቨርሲቲውን ንብረት እንዲሸጥ ይወስናል፤ ንብረቱ የማይንቀሳቀስ ንብረት ከሆነ እና መሸጥ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እንዲሸጥ በ2/3ኛ ድምፅ ይወስናል፤

፳/ የራስ ገዝ ዩኒቨርስቲው አካላትና ሌሎች አደረጃጀቶች የሚያስተላልፏቸው ውሳኔዎችና የሚፈፅሟቸው ተግባራት ሕግንና የአሰራር ሥርዓትን የተከተለ፣ የነፃነትና ተጠያቂነት ሚዛን የጠበቀ ስለመሆኑ ይከታተላል፤ ግድፈቶች ሲኖሩ እንዲስተካከሉ ያደርጋል፤

፳፩/ ሌሎች ከዚህ አዋጅ ጋር የሚጣጣሙ እና የዩኒቨርሲቲውን ዓላማ ለማሳካት አመቺ የሆኑ ተግባራትን ያከናውናል፤

፳፪/ በዚህ አንቀፅ ከተሰጡት ተግባራትና ኃላፊነቶች ለራስ-ገዝ ዩኒቨርስቲው ኤግዚኪዩቲቭ ኮሚቴ፣ ማኔጂንግ ካውንስል፣ ለፕሬዚዳንቱ በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

## ፲፬. የቦርድ ስብሰባዎች

፩/ የቦርዱ ስብሰባ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ የሚካሄድ ይሆናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የቦርዱ ሰብሳቢ አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን ወይም በአምስት የቦርድ አባላት በጽሁፍ ሲጠየቅ አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል፡፡

## ፲፭. ስለፕሬዝዳንት ሹመት

፩/ ፕሬዚዳንቱ የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ነው፡፡

፪/ ፕሬዚዳንቱ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ግልፅ በሆነ ውድድር የምልመላና ምርጫ ኮሚቴ ተቋቁሞ፣ ኮሌጆችና ትምህርት አሀዶች በተሳተፉበት የምልመላና ነፃ የምርጫ ሥርዓት ተመዝኖ፣ ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ሶስት እጩዎች በቦርድ ተጨማሪ ግምገማ ተካሂዶ በዩኒቨርሲቲው ቻንስለር የሚሾም ሲሆን፣ ዝርዝሩ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

18/ Grant permission, decied for out of court settlement through arbitral tribunal; and approve the same;

19/ Decide on the sale of autonomous university assets; however, when the asset disposal relates to immovable property and found necessary to sell the decision to sale shall be supported by a two-third majority;

20/ Monitor whether the decisions and other activities of the university bodies and other organs are accountable and in accordance with laws and working procedures; and rectify breaches;

21/ Perform other activities compatible with this Proclamation and relevant for the attainment of the objectives of the University;

22/ Delegate any of its powers and responsibilities under this Article to the Executive Committee; Managing Council or the President of the Autonomous University.

## 14. Sessions of the Board

1/ The Board shall meet at least once in a month.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, when necessary the Chairperson of the Board shall convene a meeting or when five members of the Board request it in writing.

## 15. Appointment of the President

1/ The President shall be the Chief Executive Officer of the Autonomous University.

2/ The President shall be appointed by the Chancellor up on submission by the Board of three candidates elected on the basis of international open competition through the process that shall involve establishment of screening and selection committee and the participation of colleges and academic units. Details shall be determined by the Directives of the Board.

፫/ ፕሬዚዳንቱ ቢያንስ የሚከተሉትን መስፈርቶች ያሟላ መሆን አለበት፡-

ሀ) የዩኒቨርሲቲውን ዓላማዎች ለማሳካት የሚያስችል ችሎታና ቁርጠኝነት፤

ለ) የተረጋገጠ የመሪነትና የማስተዳደር ብቃት ፤ እና

ሐ) በውድድር ካሸነፈ እና የፖለቲካ ፓርቲ አባል ከሆነ ከፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ለመልቀቅ የተስማማ መሆን፡፡

፬/ የፕሬዚዳንቱ የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ሲሆን ለተጨማሪ አንድ የሥራ ዘመን ብቻ ሊወዳደር ይችላል፡፡

**፲፮. <u>የፕሬዚዳንቱ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

ፕሬዚዳንቱ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩/ በቦርድና ሴኔት የሚወጡም ሆኑ የሚሰጡ የሥራ አቅጣጫዎችን ፣ መመሪያዎችን ፣ ውሳኔዎችን እና ሌሎች የሚሰጡት ተግባራትን ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፤

፪/ ከሚመለከታቸው የአካዳሚክ ክፍሎች ጋር በመመካከር በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ ካሉ አግባብነት ያላቸው ተቋማት ጋር ስምምነት ያደርጋል፤

፫/ ምክትል ፕሬዚዳንቶች በብቃት ማነስ፣ በዲሲፕሊን እና በሌሎች በቂ ምክንያቶች ከኃላፊነታቸው ሊነሱ ይገባል ብሎ ካመነ እንዲነሱ ለቦርዱ ያቀርባል፤

፬/ የዩኒቨርሲቲውን የስራ ክንውን ሪፖርት ለሴኔትና ለቦርዱ ያቀርባል፤

፭/ የበጀት ዓመቱ ባለቀ ሦስት ወር ጊዜ ውስጥ የዩኒቨርሲቲውን ዓመታዊ ሂሳብ በመዝጋት በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ዝግጁ ያደርጋል፤

፮/ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ከሶስተኛ ወገን ጋር በሚያደርገው ማናቸውም ግንኙነት ዩኒቨርሲቲውን ይወክላል፤

፯/ የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ካውንስል፣ ሴኔት፣ የማኔጂንግ ካውንስልና የኤግዚኪዩቲቭ ኮሚቴ ሰብሳቢ ይሆናል፤

3/ The President shall fulfill at least the following criteria:

a) Capacity and commitment for the attainment of objectives of the Autonomous University;

b) Demonstrated leadership ability; and

c) Shall agree to withdraw from political party membership if chose for presidency.

4/ The term office of the President shall be five years, however, he may compete for one additional term only.

**16. <u>Powers and Responsibilities of the President</u>**

The President shall have the following powers and responsibilities:

1/ Implement and ensure the implementation of guidelines, directives, decisions, and other responsibilities decided or issued by the Board and the Senate;

2/ In consultation with relevant academic units, enter into agreements with appropriate national and international organs;

3/ Request the Board for removal of Vice-Presidents for reasons of incompetence, disciplinary voilations, and other sufficient grounds;

4/ Submit performance report of the University to the Senate and the Board;

5/ Within three months of the expiry of the budget year, close the accounts of the University and make available the same for audit by the External Auditor;

6/ Represent the Autonomous University in all its dealings with third parties;

7/ Chair the meetings of the University Council, Managing Council, and Executive Committee;

፰/ በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ፲፯. ሴኔት

፩/ ቢያንስ የሚከተሉትን በአባልነት የያዘ የዩኒቨርሲቲው ሴኔት ይቋቋማል፡-

ሀ) ፕሬዚዳንት፤

ለ) ሁሉም ምክትል ፕሬዚዳንቶች፤

ሐ) የዩኒቨርሲቲው ሬጂስትራር፤

መ) የኮሌጅ ዲኖች፤

ሠ) የኢንስቲትዩት ዳይሬክተሮች፤

ረ) የዓብያተ መጻሕፍት ዋና ኃላፊ፤

ሰ) የተማሪዎች ዲን፤

ሸ) ከእያንዳንዱ ኮሌጅ አንድ የመምህራን ተወካይ፣ የማስተማሪያ ሆስፒታል ያላቸው አንድ የክሊኒካል ሠራተኛ ተወካይ፤

ቀ) ከመምህራንና የተማሪዎች ማህበራት ከያንዳንዳቸው አንድ ተወካይ እንዲሁም ከአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች አንድ ተወካይ፤

በ) የአስተዳደር ሰራተኞች አንድ ተወካይ፤

ተ) ቁጥራቸው ከሦስት ያልበለጠ ሌሎች ተጨማሪ አባላት ሊሰየሙ ይችላሉ፡፡

## ፲፰. የሴኔት ተግባርና ኃላፊነት

ሴኔት አካዳሚያዊ ጉዳዮችን በበላይነት የሚመለከት ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩/ የዩኒቨርሲቲውን አጠቃላይ የትምህርት ካላንደር ያፀድቃል፤

፪/ የትምህርት መርሃ-ግብሮችን ያፀድቃል፤

፫/ ፕሮፌሰርነትን ጨምሮ፣ የአካዳሚያውን የማዕረግ ዕድገት መሥፈርትና ሥርዓት ይወስናል፤

፬/ የፕሮፌሰርነት ማዕረግ ጥያቄን መርምሮ ተገቢነቱን ካመነ እንዲፀድቅ ለቦርዱ ያቀርባል፤

8/ Discharge other tasks assigned to him by the Board.

## 17. The Senate

1/ There shall be established the Senate of the University which shall consist of at least the following:

a) The President;

b) All Vice Presidents;

c) University Registrar;

d) Deans of Colleges;

e) Directors of Institutes;

f) Chief Librarian;

g) Dean of Students;

h) One representative of academic staff from each College; and an additional one representative of clinical staff from a teaching hospital;

i) One representative each from associations of academic staff and students; and a representative of students with disability;

j) One representative of the administrative staff;

k) A maximum of additional three members may be included.

## 18. Powers and Responsibilities of the Senate

The Senate as a supreme organ on academic matters shall have the following powers and responsibilities:

1/ Approve overall University academic calendar;

2/ Approve academic programs;

3/ Determine criteria and procedure for academic promotion including for professorship;

4/ Review request for the rank professorship and, if found valid, submit same to the Board for approval;

፭/ የክብር ዲግሪዎችን እና ሌሎች ሽልማቶችን መርምሮ ለቦርዱ ያቀርባል፤

፮/ ከምክትል ፕሬዚዳንት በታች ያሉ የአካዳሚያዊ ሹመቶችን አስመልክቶ መስፈርት ያወጣል፤

፯/ የዩኒቨርሲቲውን የዕድገት ዕቅዶችን ገምግሞ ለቦርዱ ያቀርባል፤

፰/ የተማሪ ቅበላ፣ የዲሲፕሊን እርምጃ እና ምርቃትን የሚመለከቱ በሴኔት ሕግ ይወስናል፤

፱/ የዩኒቨርሲቲውን የመማር ማስተማር፣ የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር፣ እና የማህበረሰብ ጉድኝት ተግባራት የሚመለከቱ መመሪያዎችን ያወጣል፤

፲/ ይህን አዋጅ እንዲሁም በቦርዱ የሚወጡ የአካዳሚክ ጉዳዮችን፣ የአካዳሚክ ሠራተኞችን ቅጥር፣ ዕድገት፣ ጥቅማጥቅም፣ የዲሲፕሊንና ከሥራ መሰናበት፣ የአካዳሚክ ኃላፊዎችን ምርጫ፣ የተማሪዎች አስተዳደር እና የመሳሰሉት ጉዳዮችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችንና መመሪያዎችን ለማስፈፀም የሚያስችሉ የአሰራር ሥርዓቶችን ይዘረጋል፤

፲፩/ የሴኔት ሕግ ያዘጋጃል፣ ለቦርድ አቅርቦ ያፀድቃል፡፡

## ፲፱. የሴኔት ስብሰባዎች

፩/ ሴኔቱ በዓመት ቢያንስ አራት ጊዜ ይሰበሰባል፡፡

፪/ ፕሬዚዳንቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የሴኔት ስብሰባ መጥራት ይችላል፡፡

፫/ ከሴኔት አባላት መካከል ቢያንስ ከአንድ ሶስተኛ የማያንሱት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ ፕሬዚዳንቱ የሴኔት አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል፡፡

፬/ አደረጃጀታቸውን ወክለው የሚመጡ የሴኔት አባላት የሥራ ዘመን ሶስት ዓመት ሲሆን ለአንድ ተጨማሪ የሥራ ዘመን ብቻ በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ፡፡

5/ Review honorary degrees and other awards and submit to the Board for approval;

6/ Set criteria for academic administration positions below vice-presidency;

7/ Review strategic plans of the University and submit same to the Board for approval;

8/ Determine student admission, discipline, and graduation in the Senate Legislation;

9/ Issue guidelines on activities pertaining to teaching-learning, research and technology transfer, and community engagement;

10/ Establish working procedure to implement this Proclamation as well as Policies and Directives issued by the Board relating to academic matters, academic staff employment, promotion, benefits, discipline, termination, selection of academic officials, student administration, and related matters; and

11/ Prepare Senate Legislation for approval by the Board.

## 19. Sessions of the Senate

1/ The Senate shall convene at least four times a year.

2/ The President may convene the Senate at any time he thinks necessary.

3/ The President shall convene the Senate where at least one-third of Senate members request for the meeting.

4/ The duration of service of representative members in the Senate shall be three years, with the possibility of reelection only for one term.

## ፳. የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ካውንስል

፩/ የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንቶች፣ በምክትል ፕሬዚዳንትነት ማዕረግ የተለዩ የኮሌጅና የኢኒስቲቲዩት ኃላፊዎች፣ የኮሌጅ ዲኖች፣ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች፣ የሰው ሀብት አስተዳደር ኃላፊ፣ የሕግ አገልግሎት ኃላፊ፣ የፋይናንስ አስተዳደር ኃላፊ፣ የግዥ አስተዳደር ኃላፊ፣የንብረት አስተዳደር ኃላፊና ሌሎች በቦርድ የሚለዩ አባላት ያሉበት የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ካውንስል ይቋቋማል።

፪/ የራስ ገዝ ዩኒቨርስቲው ካውንስል ዩኒቨርሲቲውንና የአሀዶቹን አፈፃፀም ይገመግማል፡፡

፫/ ሌሎች በቦርድ የሚሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች ይፈፅማል።

## ፳፩. የማኔጅንግ ካውንስል

፩/ የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንቶች፣ በምክትል ፕሬዚዳንትነት ማዕረግ የተለዩ የኮሌጅና የኢንስቲትዩት ኃላፊዎች፣ የኮሌጅ ዲኖች፣ የሰው ሀብት አስተዳደር ኃላፊ፣ የሕግ አገልግሎት ኃላፊ፣ የፋይናንስ አስተዳደር ኃላፊ፣ የግዥ አስተዳደር ኃላፊና የንብረት አስተዳደር ኃላፊ ያሉበት የማኔጅንግ ካውንስል ይቋቋማል።

፪/ በቦርድና በሴኔት የሚፀድቁና የሚወሰኑ መመሪያዎችን ፣ ፖሊሲዎችን እና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች ሲዘጋጁ አዳብሮ እንዲፀድቁ ያቀርባል፡፡

፫/ ሌሎች በቦርድ የሚሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች ይፈፅማል።

## ፳፪. ኤግዚክዩቲቭ ኮሚቴ

፩/ የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ፣ምክትል ፕሬዝዳንቶች ፣ በምክትል ፕሬዝዳንትነት ማዕረግ የተለዩ የኮሌጅና የኢኒስቲትዩት ኃላፊዎች አባላት ያሉት ኤግዚክዩቲቭ ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡

## 20. Autonomous University Council

1/ There shall be established the Autonomous University Council composed of the President, Vice-Presidents, Officials of Colleges and Institutes with the status of Vice President, College Deans, Heads of Departments and Schools, Head of Human Resources, Head of Legal Services, Head of Financial Administration, Head of Procurement Services, Head of Property Administration and other members to be identified by the Board.

2/ It shall evaluate the performance of the University and its academic units.

3/ It shall discharge other responsibilities tasked to it by the Board as well.

## 21. Managing Council

1/ There shall be established the Autonomous University Managing Council composed of University President, Vice-Presidents, Officials of Colleges and Institutes with the status of Vice Presidents, College Deans, Head of Human Resources, Head of Legal Services, Head of Financial Administration, Head of Procurement Administration, and Head of Property Administration.

2/ It shall prepare and submit draft Directives, Policies, and other instruments to be decided or approved by the Board or the Senate.

3/ It shall discharge other responsibilities tasked to it by the Board as well.

## 22. Executive Committee

1/ There shall be established the Autonomous University Executive Committee composed of University President, Vice-Presidents, and Officials of Colleges and Institutes with the status of Vice President.

፪/ የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት በቦርድ ይወሰናል፡፡

## ፳፫. ምክትል ፕሬዝዳንቶች

፩/ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ተጠሪነታቸው ለፕሬዚዳንቱ የሆነ፣ ምክትል ፕሬዚዳንቶች እና በምክትል ፕሬዚዳንት ማዕረግ የሚለዩ ኃላፊዎች ይኖሩታል፡፡ ምክትል ፕሬዚዳንቶች ከአካዳሚያዊ ሠራተኞች በውድድር የሚመረጡ ይሆናል፡፡

፪/ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው የሚኖሩት የምክትል ፕሬዚዳንቶች ብዛትና ተግባር እና ኃላፊነታቸው በቦርዱ ይወሰናል፡፡

፫/ ምክትል ፕሬዚዳንቶች ኮሌጆችና ትምህርት ክፍሎች በተሳተፉበት ምልመላና ምርጫ የሚሾሙ ሲሆን ዝርዝሩ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፬/ የምክትል ፕሬዚዳንት የስራ ዘመን አራት ዓመት ሆኖ ለተጨማሪ አንድ የሥራ ዘመን ብቻ ሊወዳደር ይችላል፡፡

## ፳፬. ሌሎች ኃላፊዎች

፩/ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው እንደአስፈላጊነቱ የኮሌጅ ኃላፊዎች፣ ኦፊሰሮች፣ ዳይሬክተሮች፣ ሬጅስትራር እና የተለያዩ የትምህርት፣ የምርምር፣ የማህበረሰብ ጉድኝት እና የአስተዳደር ክፍል ኃላፊዎች ይኖሩታል፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽፅ (፩) የተጠቀሱት ኃላፊዎች የአመራረጥ ሥርዓት፣ ተግባርና ኃላፊነት፣ የስራ ዘመንና ጥቅማ ጥቅም ቦርድ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

# ክፍል ሦስት

# አካዳሚያዊ እና ተቋማዊ ነፃነት

## ፳፭. አካዳሚያዊ ነጻነት

፩/ ማንኛውም ራስገዝ ዩኒቨርሲቲ በተልዕኮውና በዓለም አቀፍ መልካም ልምድ መሠረት አካዳሚያዊ ነፃነት ይኖረዋል፤

2/ The Board shall determine the powers and responsibilities of the Executive Committee.

## 23. Vice Presidents

1/ The Autonomous University shall have Vice Presidents and Officials with the status of Vice President accountable to the President. The Vice Presidents shall be elected from the academic staff based on transparent and competitive process.

2/ The Board shall determine the number, powers and responsibilities of Vice-Presidents.

3/ The Vice-Presidents shall be elected through a process of screening and selection and with the participation of colleges and other academic units. details shall be determined with Directive issued by the Board.

4/ The term office of a Vice-President shall be four years. He might compete for one additional term only.

## 24. Other Officers of the University

1/ The Autonomous University shall have College Deans, Officers, Directors, Registrar and Officials of the various teaching, research, community engagement and administrative offices as necessary.

2/ The Directives of the Board shall determine the appointment procedure, powers and responsibilities, duration of service, and benefits of the Officials enumerated under Sub-Article (1) of this Article.

# PART THREE

# ACADEMIC AND INSTITUTIONAL AUTONOMY

## 25. Academic Autonomy

1/ Any Autonomous University shall enjoy academic autonomy in accordance with its mission and international good practices.

፪/ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው አካዳሚያዊ ነፃነቱን ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም ከዓለም አቀፍ በጎ ልምድ ጋር በተጣጣመ መልኩ መተግበር አለበት።

**፳፮. ተቋማዊ ነፃነት**

፩/ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው በዚህ አዋጅ እና አዋጁን ተከትሎ በሚወጣ ደንብና ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የውስጥ አስተዳደርን በራስ የመወሰን፣ አስተዳደራዊ መዋቅሮችን የመዘርጋት፤ የትምህርት መርሀ-ግብሮችን የመቅረፅ፤ ሥርዓተ ትምህርትን የማዘጋጀትና የማፅደቅ፣ የምርምር ዘርፎችን መለየትና ቅደም ተከተላቸውን የመወሰን፤ የተማሪዎች ቅበላ መስፈርት አዘጋጅቶ የመቀበል፣ የገንዘብ ምንጮቹን የማፈላለግና አጠቃቀሙን የመወሰን፤ ንብረት የማፍራት፣ በዚህ አዋጅ መሠረት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ ሠራተኞችን የመቅጠርና የማስተዳደር፣ነፃነት አለው።

፪/ ራስ-ገዝ ዩኒቨርሲቲው ነፃነቱን የሚተገብረው ሕጋዊነትን፣ ውጤታማነትን፣ ቅልጥፍናን፣ ግልፀኝነትን፣ ፍትሃዊነትንና ተጠያቂነትን ባረጋገጠ መልኩ መሆን ይኖርበታል፡፡

፫/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) በዚህ አዋጅ መሠረት በራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ላይ የሚደረግ ክትትልና ቁጥጥርን የሚያስቀር አይሆንም።

**፳፯. የአካዳሚያዊ አሀዶች ነፃነት**

የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ አካዳሚያዊ አሀዶች ዓላማቸውን ለማሳካት የትምህርት ፕሮግራሞችንና የምርምር አቅጣጫን የመወሰን፣ የፋይናንስና ንብረት ማስተዳደር፣ እና ሌሎች አስፈላጊ ተግባራትን የማከናወን ነፃነት እንዲኖራቸው ዝርዝሩ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል አራት

## የትምህርት መርሃ-ግብሮች፣ ምርምርና የማኅበረሰብ ጉድኝት

2/ An Autonomous University shall exercise its autonomy in consonance with this Proclamation and international good practices

**26. Institutional Autonomy**

1/ In accordance with this Proclamation and the Regulation to be issued on basis of this Proclamation as well as the Directives to be issued by the Board; an Autonomous University shall have the autonomy to determine by itself its internal administration, determine its administrative structure, design educational programs, formulate curricula and approve them, determine and prioritize areas of research, admit students pursuant to the criteria it formulates for admission, seek sources for its finance and determine its use, own property and sell and replace such property, and to employ and administer its staff.

2/ An Autonomous University shall exercise its autonomy in such a way that rule of law, productivity, efficiency, transparency, justice and accountability are ensured.

3/ Sub Article (1) of this Article shall not do away with the supervision and follow-up to be conducted on an Autonomous University.

**27. Autonomy of Academic Units**

Academic units of an Autonomous University shall have internal autonomy necessary for the attainment of their objectives including determination of their educational programs, identification of research directions, administration of finance and property and other necessary activities. Details shall be provided by the Directives to be issued by the Board.

## PART FOUR

## EDUCATIONAL PROGRAMS, RESEARCH AND COMMUNITY ENGAGEMENT

**፳፰. <u>የትምህርት ፕሮግራሞች</u>**

፩/ ማንኛውም ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ በመደበኛ፣ በተከታታይ ትምህርት፣ በርቀት ወይም በመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ የሚታገዝ ትምህርት መስጠት ይችላል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ ሥር በተቀመጡት መንገዶች ሊሰጡ የሚችሉ የትምህርት ዓይነቶችን መሥፈርቶች በመመሪያ ይወስናል፡፡

፫/ ማንኛውም ብቃት ያለው መሆኑ የተረጋገጠለት ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ በተጨማሪ የማስፈፀም አቅምን ለመገንባት ወይም በአንድ የተወሰነ የሙያ መስክ ከተቋሙ ተልዕኮና ከሚሰጣቸው ፕሮግራሞች ጋር ተያያዥነት ባላቸው መስኮች ላይ ዕውቀትና ክህሎትን ለማስተላለፍ አጫጭር ስልጠናዎችን በመስጠት ተገቢውን ሰርተፊኬት መስጠት ይችላል፤ የሰርተፍኬት ደረጃዎች፣ የጊዜ እርዝማኔ እና የክሬዲት መጠን ሥርዓት በቦርዱ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፳፱. <u>የማስተማሪያ ቋንቋ</u>**

፩/ ከቋንቋ ትምህርቶች ውጭ የራስ ገዝ ዩኒቨርስቲው የማስተማሪያ ቋንቋ እንግሊዝኛ ነው፡፡

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ለአጫጭር ስልጠና እና ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት መምህራን ማዘጋጃ የሚፈፀም ሙያዊ ስልጠና በተፈላጊው ቋንቋ ሊሰጥ ይችላል።

፫/ መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የሚሰጥ ትምህርት በምልክት ቋንቋ መሰጠት ወይም መደገፍ አለበት፡፡

**፴. <u>ሥርዓተ ትምህርት</u>**

፩/ የማንኛውም ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ የሥርዓተ ትምህርት ቀረፃ፣ ትግበራና የምዘና ዓላማ ተማሪው ተገቢው ሳይንሳዊ እውቀት፣ በነፃነት የማሰላሰል ክህሎት፣ ሀሳቡን የመግለፅ ብቃት ኖሮት ሙያዊና ተግባራዊ እሴቶችን እንዲጨብጥ በማስቻል ብቁ ባለሙያን ማዘጋጀት ይሆናል፡፡

**28. <u>Educational Programs</u>**

1/ An Autonomous University may offer regular, continuing, distance, or information-technology assisted educational programs.

2/ The Ministry shall determine by Directives types and requirements of the educational programs that may be offered using any of the modalities under Sub-Article (1) of this Article.

3/ Any Autonomous University with approved competence may offer short-term trainings for capacity building or transfer of knowledge and skills in specific fields and areas of its specialization. The Directives of the Board shall determine, the duration of such trainings and the credit system and the level of certification.

**29. <u>Medium of Instruction</u>**

1/ The medium of instruction, except in language studies, shall be the English language.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, short term trainings or programs designed for preparation of teachers for primary schools may be given in other appropriate languages.

3/ Education for students with hearing impairment shall be administered or accompanied by sign language.

**30. <u>Curriculum</u>**

1/ Curricular design, delivery, and assessment of learning outcomes in any Autonomous University shall aim at enabling the learner to acquire pertinent scientific knowledge, independent thinking abilities, communication skills, and professional and practical values that together make competent professional.

፪/ የሥርዓተ ትምህርት ቀረፃና ትግበራ በጥናት ላይ የተመሠረተ፣ ወቅታዊና አግባብነት ያለው መሆን ይኖርበታል።

**፴፩. ስለ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ትምህርት ጥራት ማጎልበት ሥርዓት**

፩/ ራስ-ገዝ ዩኒቨርሲቲ በየጊዜው የሚሻሻል የጥራት ማጎልበቻ ሥርዓት ይኖረዋል፡፡

፪/ የጥራት ማጎልበቻ ሥርዓቱ የአካዳሚያዊ ሠራተኞች የሙያ ልማትን፣ የትምህርት ይዘትን፣ የመማር ማስተማር ሂደትን፣ የተማሪዎች ብዛትን፣ የተማሪዎች ምዘናና ውጤት አሰጣጥን እንዲሁም ተማሪዎች በይዘቱ ላይ ሀሳብ ሊሠጡ የሚችሉበት፣ ግልፅና የተሟላ የጥራት መለኪያን የያዘ መሆን ይኖርበታል፡፡

፫/ የጥራት ማጎልበቻ ሥርዓቱ ከአመልካች ተማሪ እስከ ሥራ ላይ ያሉ ተመራቂ ተማሪዎችን ግምገማ ያካተተ ይሆናል፡፡

፬/ ራስ-ገዝ ዩኒቨርሲቲው ጥራት ማጎልበትን አስመልክቶ የሚመለከተው የጥራት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን የሚሰጣቸውን ምክረ-ሀሳቦች ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

፭/ ማንኛውም ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ የሚመለከተው ጥራትን የሚቆጣጠር ባለስልጣን የሚያስቀምጣቸውን ዝቅተኛ የጥራት ደረጃዎች የማሟላት ግዴታ አለበት።

፮/ የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የከፍተኛ ትምህርት አዋጁ አንቀፅ ፳፩ ድንጋጌዎች እንደአግባብነታቸው ተፈፃሚ ይሆናሉ።

**፴፪. ስለ አካዳሚያዊ ምክርና ድጋፍ**

፩/ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው በትምህርት አሀዶች አማካኝነት የትምህርት መስኮች ምርጫን አስመልክቶ ለተማሪዎች የቅድመ እና ድህረ ቅበላ የማማከር አገልግሎት ሥርዓትን ይዘረጋል፡፡

፪/ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎች የአካዳሚያዊ የምክርና የድጋፍ አገልግሎት ይሰጣል፡፡

2/ Curricular design and delivery shall rely on studies, be up-to date and relevant.

**31. Autonomous University Education Quality Enhancement System**

1/ The Autonomous University shall have an internal system for quality enhancement that shall be continuously revised.

2/ The internal system of quality enhancement shall provide for clear and comprehensive measures of quality covering professional development of academic staff, education content, teaching-learning process, student size, student assessment and grading, and student feedback.

3/ The quality enhancement system shall include assessments from potential applicants up to graduating students.

4/ Every Autonomous University shall be responsible to give effect to appropriate recommendations on quality enhancement by the Education and Training Authority.

5/ Every Autonomous University shall fulfill the minimum requirement for educational quality stipulated by the relevant quality assurance organ.

6/ Without prejudice to the provisions of this Article, the provisions of Article 21 of the Higher Education Proclamation shall be applicable as appropriate.

**32. Academic Guidance and Counseling**

1/ Through its academic units, the Autonomous University shall set up a system of guidance and counseling for students' choice of field of studies pre- and post-admission.

2/ The Autonomous University shall provide academic guidance and counseling services to its students.

፫/ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ልዩ አካዳሚያዊ ድጋፍ የሚያሻቸው ተማሪዎችን የሚደግፍበትና የሚያበቃበት ሥርዓት የመዘርጋት ግዴታ አለበት፡፡

፬/ ራስ-ገዝ ዩኒቨርሲቲው ልዩ ፍላጎት ያላቸው ወይም ልዩ አካዳሚያዊ ድጋፍ የሚያሻቸውን ተማሪዎች የሚደግፍበትና የሚያበቃበት ሥርዓት የመዘርጋት ግዴታ አለበት፡፡

## ፴፫. ምርምርና የምርምር አቅጣጫዎች

፩/ የሰውን ልጅ ዕውቀት ለማሳደግና ሳይንሳዊ ዳራን ለማስፋት መሠረታዊ ምርምርን ከማካሄድ በተጨማሪ፣ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው የሚያካሂደው ምርምር የትምህርት አግባብነትና ጥራትን በማሳደግ፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር እና ማኅበረሰብ ጉድኝት ላይ በተመሠረቱ የሀገሪቱ የልማትና ዕድገት ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ይሆናል፡፡

፪/ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው የራሱን ምርምር ለማካሄድና የምርምር ፕሮጀክቶችን ከሌሎች ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ተቋማት፣ የምርምር አካላት እና ኢንዱስትሪዎች ጋር በጋራ ለማካሄድ የሚያስችለው ተቋማዊ ሥርዓት ይኖረዋል፣ የምርምር ጥራት ማስጠበቂያ መንገድ ይዘረጋል።

## ፴፬. የምርምርና ፈጠራ ፈንድ

ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ፡-

፩/ የምርምርና ፈጠራ ፈንድ ይኖረዋል፣

፪/ ለምርምር የተመደበውን ፈንድ ወይም ገንዘብ በአግባቡ ለምርምር ሥራው ማዋል አለበት፡፡ የፈንዱ ምንጭ ከመንግስት ወይም መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ሊሆን ይችላል፣

፫/ ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው የምርምርና ፈጠራ ፈንድ አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት ይኖረዋል፡፡

## ፴፭. የማኅበረሰብ ጉድኝት

ራስ ገዝ ዩኒቨርስቲው ከመማር ማስተማርና ከምርምር በተጨማሪ በማኅበረሰብ ጉድኝት ላይ በመሥራት የማህበረሰብ ልማትና ዕድገት እንዲረጋገጥ ይሰራል፣ ዝርዝሩ ቦርድ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

3/ The Autonomous University shall take appropriate actions for students requiring special academic support.

4/ The Autonomous University shall take appropriate actions for special need students or students requiring special academic support

## 33. Research and Research Direction

1/ In addition to fundamental research aimed at expansion of human knowledge, the research endeavor of the Autonomous University shall focus on enhancing the relevance and quality of education and the country’s development and growth that rely on technology transfer and community engagement.

2/ The Autonomous University shall have an institutionalized system for undertaking its own researches; and undertaking joint research projects with national and international institutions, research organizations, and industries; and it shall lay down a quality assurance system for research.

## 34. Research and Innovation Fund

The Autonomous University shall:

1/ have a Research and Innovation Fund;

2/ ensure that research funds are utilized exclusively for research purposes. The source of such funds can be from governmental or non-governmental bodies;

3/ have a transparent and accountable system of research fund management and utilization.

## 35. Community Engagement

In addition to teaching-learning and research, the university shall take part in community engagement. Directives of the Board shall determine the details.

**፴፮. የማማከር አገልግሎት እና ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራት**

፩/ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ልዩ ብቃት ባካበተበት ዘርፍ የማማከር አገልግሎትና ተጓዳኝ ተግባራት ሊያከናውን ይችላል፡፡

፪/ የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው አካዳሚያዊ ሠራተኞቹ የሚያካሂዱት የማማከር አገልግሎትና ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራት ሕግንና የሥነ-ምግባር መርሆዎችን የተከተለ መሆኑን፣ መደበኛውን ሥራዎቻቸውን ፣ የተቋቋመበትን ዓላማ በማይጎዳና የትምህርት ጥራቱን በማያጓድል መንገድ መከናወናቸውን ያረጋግጣል፡፡

፫/ የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ከኢንዱስትሪዎች ጋር ግልፅነት ያለው ድርድርና ስምምነት በማድረግ መርህን የጠበቀና የጋራ ጥቅምን የሚያራምድ ግንኙነት የመመሥረት ኃላፊነት አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## የገንዘብ ምንጮች፣ የገንዘብ አስተዳደር፣ የሂሳብ መዝገብ ስለመያዝ እና ኦዲት

**፴፯. የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው የገቢ ምንጮች**

፩/ የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ የገቢ ምንጮች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ/ በስጦታ፣ በኑዛዜ፣ በአደራና በኢንዶውመንት መልክ የሚደረጉ ችሮታዎች፤

ለ/ የተማሪዎች የምዝገባ ክፍያን ጨምሮ የትምህርት ክፍያ፤

ሐ/ ከፓተንት፣ ከፈጠራና ከቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራ የሚገኙ ገቢዎች፤

መ/ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚገኙ ገቢዎች፤

ሠ/ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ሊሰራቸው ከሚችላቸው የንግድ እና ኢንቨስትመንት ሥራዎች የሚገኙ ገቢዎች፤

ረ/ ከመንግሥት የሚሰጥ ድጋፍ፤ እና

ሰ/ ከሌሎች ምንጮች የሚገኝ ገቢ፡፡

**36. Consultancy and other Supplementary Activities**

1/ The Autonomous University may perform consultancy or other supplementary tasks in areas of its specialization.

2/ The Autonomous University shall ensure that consultancy or other supplementary tasks undertaken by its academic staff comply with the relevant laws and ethical principles and do not compromise regular duties of the staff concerned, the University's objectives and quality of education.

3/ The Autonomous University shall have the responsibility to establish linkage with various industries for mutual benefits based on principles and transparent negotiations and agreements.

## PART FIVE

## SOURCES OF FINANCE, FINANCIAL ADMINISTRATION, KEEPING BOOKS OF ACCOUNT AND AUDIT

**37. Sources of Income of an Autonomous University**

1/ Sources of income of an Autonomous University shall be the following:

a) Charities in the form of donation, inheritance, trusteeship and endowment;

b) From charges for education including registration fees;

c) Income generated from patents, innovation and technology transfer;

d) Incomes generated from services rendered by the university;

e) Incomes generated from commercial and investment activities that may be carried out by the university;

f) Grants from the government; and

g) Incomes from other sources.

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው የሚያገኘው ገቢ ለራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ተልዕኮ ማስፈፀሚያ የሚውል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አጠቃቀሙ እና አስተዳደሩ መሠረታዊ የፋይናንስ መርሆዎችን መሠረት በማድረግ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

**፴፰. በመንግሥት ስለሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ፣ አጠቃቀምና ክትትል ሥርዓት**

፩/ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው በሂደት ራሱ በሚያመነጨው ሀብት ወጪዎችን የሚሸፍንበትን ሥርዓት እየገነባ መሄድ ያለበት ሲሆን በፋይናንስ ራሱን እስኪችል ድረስ በሂደት እየቀነሰ የሚሄድ የገንዘብ ድጋፍ ከመንግሥት በብሎክ ግራንት ሥርዓት ይመደብለታል።

፪/ ከመንግሥት የሚጠበቀው የበጀት ድጋፍ፡-

ሀ. ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን እና አካታችነትን ለማረጋገጥ የመግቢያ መስፈርት አሟልተው የትምህርት ወጪያቸውን መሸፈን የማይችሉ ተማሪዎችን፣

ለ. በማስተማሪያ ሆስፒታሎች በሕግ አግባብ በነፃ መሰጠት ያለባቸውን የህክምና አገልግሎቶችንና በነፃ ህክምና ማግኘት ያላባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች፣

ሐ. ራስ ገዝ ዩኒቨርስቲዎች የሚያከናውኗቸውን ጥናትና ምርምር፣ ማህበረሰብ ጉድኝትና ብቁ ተቋማትን መገንባት፤

ታሳቢ ያደረገ ሆኖ ዝርዝሩ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።

**፴፱. ስለሚቋቋሙ የንግድ ድርጅቶች**

፩/ ማንኛውም ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ በቦርዱ ውሳኔ የንግድ ድርጅቶች ሊያቋቁም ይችላል።

2/ Without prejudice to the fulfilment of the requirement that the autonomous university shall only utilize its incomes to fulfill its objectives; the use and administration of the incomes stated in Sub-Article (1) of this Article shall be in accordance with the Directives to be issued by the Board based on basic financial principles.

**38. Utilization and Monitoring of Funds Granted by the Government**

1/ Whilst an Autonomous University shall see to it that it shall have to establish a system whereby it shall cover all its expenditures from the incomes it generates; the Government shall allocate funds by way of block-grants for the university till the university reaches the stage of financial self-sufficiency.

2/ Budgetary support expected from the Government shall take into consideration the following the details of which shall be determined by the Regulation to be issued by the Council of Ministers:

a) Ensuring equitable uses and inclusivity to students that are unable to pay for their education after having fulfilled entrance requirements;

b) Free medical services to be provided by teaching hospitals to members of the society entitled to get free medication in accordance with law;

c) Research conducted by Autonomous Universities, community engagements and the building of competent institutions.

**39. Commercial Enterprises to be Established**

1/ Any Autonomous University may, pursuant to the decision of the Board, establish commercial enterprises.

፪/ የንግድ ድርጅቶች የራሳቸው የተለየ ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ሆነው በንግድ ሕግና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎጋት መሠረት ይቋቋማሉ፡፡

## ፵. የሒሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ

፩/ ማናቸውም ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ የገንዘብ እንቅስቃሴ የሚያሳይ ተቀባይነት ባለው የሒሳብ አሰራር የተዘጋጀ የሒሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ አለበት።

፪/ የሒሳብ ሰነዶቹ የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲውን ገቢና ያወጣውን ወጪ፣ የወጪውን ምክንያት፣ ሀብትና ዕዳ፣ የለጋሾችን ማንነትና የገቢውን ምንጭ ያካተቱ መሆን አለባቸው።

፫/ በዚህ አንቀፅ መሠረት የተዘጋጁ የሒሳብ ሰነዶች የሒሳብ ዓመቱ ካለቀ በኋላ ቢያንስ አስር ዓመት ተጠብቀው መቆየት አለባቸው።

፬/ የራስ ገዝ ዩኒቨርስቲው ቦርድ የዩኒቨርስቲው ሀብት ምንጭና አጠቃቀምን በተመለከተ በተለያዩ አማራጮች ለዩኒቨርስቲው ማህበረሰብና ለህዝብ ተደራሽ ስለሚሆንበት መንገድ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

## ፵፩. ዓመታዊ የሒሳብ መግለጫና ምርመራ

፩/ ማንኛውም ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ተቀባይነት ባላቸው መመዘኛዎች መሠረት የተዘጋጀ ዓመታዊ የሒሳብ መግለጫ ለገንዘብ ሚኒስቴር መላክ አለበት።

፪/ የማንኛውም ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ሒሳብ በየዓመቱ በፌደራል ዋና ኦዲተር መመርመር አለበት።

## ክፍል ስድስት

## የአስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር

## ፵፪. የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር

በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው አግባብነት ባላቸው ህጎች ስለ ከፍተኛ ትምህርት

2/ Commercial Enterprises shall have independent legal personality and shall be established in accordance with the Commercial Code and other relevant laws.

## 40. Duty to Keep Books of Account

1/ Every Autonomous University shall keep books of account showing financial flow in the institution prepared in accordance with acceptable accounting methods.

2/ Books of account shall include incomes and expenditures of the autonomous university, reasons for expenditures, assets and liabilities, identity of donors and sources of incomes.

3/ Books of account prepared pursuant to this Article shall be preserved for a minimum of ten years after the end of the relevant fiscal year.

4/ The Board of an Autonomous University shall establish various alternative mechanisms via which the sources and utilization of the assets of the university shall be disclosed to the university community and the general public.

## 41. Annual Financial Statements and Audit

1/ Every Autonomous University shall submit to the Ministry of Finance annual financial statements prepared in accordance with acceptable accounting methods.

2/ The books of account of every autonomous university shall be audited annually by the Federal General Auditor.

## PART SIX

## POWERS AND RESPONSIBILITIES OF EXECUTIVE ORGANS

## 42. Powers and Responsibilities of the Ministry

Without prejudice to powers and responsibilities given to it by other provisions of this Proclamation, powers and

ተቋማት ለሚኒስቴሩ የተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች እንደአግባብነታቸው በራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

፵፫. **የትምህርትና ሥልጠና ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነት**

የትምህርትና ስልጠና ባለሥልጣን ከከፍተኛ ትምህርት እና ስልጠና ጋር በተገናኘ በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው በሌሎች ሕጎች የተሰጡትን ተግባርና ኃላፊነቶች ከዚህ አዋጅ ጋር በተጣጣመ መልኩ በራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲዎች ላይ ተግባራዊ ያደርጋል።

## ክፍል ሰባት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፵፬. **የስብሰባና ውሳኔን የማሳለፍና የምልዓተ ጉባዔ ሥነ-ሥርዓት**

፩/ በየትኛውም ደረጃ ባሉ የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው አካላት የሚካሄዱ ስብሰባዎችና የሚተላለፉ ውሳኔዎች ከራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ካውንስል ስብሰባ በስተቀር በስብሰባው ጸሐፊ በቃለ ገባዔ ተይዘው በሁሉም አባላት መፈረም ይኖርባቸዋል፡፡ ቃለ ጉባዔዎች አርካይቭ የሚደረጉ ሲሆን እንዳስፈላጊነቱ ለራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ተደራሽ ይሆናሉ፡፡

፪/ በልዩ ሁኔታ ካልተቀመጠ በቀር ሁሉም ውሳኔዎች የሚተላለፉት ድምፅ መስጠት በሚችሉ አባላት በድምፅ ብልጫ ይሆናል፡፡

፫/ ድምፅ እኩል በእኩል ሲሆን ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡ ይሁንና ድምፅ ያልሰጡ አባላት ቁጥር የውሳኔ ሀሳቡን በመደገፍ ድምፅ ከሰጡት የበለጠ ከሆነ ጉዳዩ እንደገና ይታያል፡፡

፬/ በማንኛውም ስብሰባ ላይ ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

፵፭. **ደንብና መመሪያ ስለማውጣት**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

responsibilities entrusted to the Ministry by other laws regulating higher education institutions shall as appropriate to be applicable on Autonomous Universities.

43. **Powers and Responsibilities of the Education and Training Authority**

Without prejudice to powers and responsibilities given to it by other provisions of this Proclamation, the powers and responsibilities given by other laws to Education and Training Authority shall apply to Autonomous Universities in ways consistent with this Proclamation.

## PART SEVEN
## MISCILLANEOUS PROVISIONS

44. **Meetings, Decision Making Procedures, and Quorum**

1/ Except for the meetings of the Council of an Autonomous University, meetings and decisions made by any organ of the university shall be recorded in the form of minutes by the secretary and signed by all members. The minutes shall be archived and be made accessible, as necessary, to the community of the Autonomous University.

2/ Unless otherwise provided, all decisions shall be made by a simple majority of members present and voting.

3/ In the event of a tie, the Chairperson shall have a casting vote. However, if the number of abstainers is more than the majority who voted for a motion, the matter shall be presented for reconsideration.

4/ In any meeting, there shall be a quorum when more than half the members are present.

45. **Issuance of Regulations and Directives**

1/ The Council of Ministers may issue Regulations for the implementation of this Proclamation.

፪/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት የሚወጣውን ደንብ ለማስፈፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

## ፵፮. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

፩/ ማንኛውም ዩኒቨርሲቲ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ሆኖ ከተቋቋመ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ሆኖ ከመቋቋሙ በፊት በመንግሥት የተመደበለት በጀት እና ሌላ ማንኛውም ቋሚ ሀብት ወደ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ይተላለፋል።

፪/ ማንኛውም ዩኒቨርሲቲ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ሆኖ ከተቋቋመ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ሆኖ ከመቋቋሙ በፊት ዩኒቨርሲቲው ያለበት ዕዳ ወይም ግዴታ ወደ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ይተላለፋል።

፫/ ማንኛውም ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ተቋቁሞ ተቋማዊ እና አካዳሚያዊ ነፃነቱን ለመተግበር አቅም እስከሚፈጥርበት ጊዜ ያለው የሽግግር ጊዜ በከፍተኛ ትምህርት አዋጁ መሠረት እንደማንኛውም ዩኒቨርሲቲ ሥራውን እንዲቀጥል ሚኒስቴሩ ሊወስን ይችላል።

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) መሠረት የሚኖረው የሽግግር ጊዜ ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲው ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ከሁለት ዓመት ሊበልጥ አይችልም።

## ፵፯. ተፈፃሚነት ስለሌላቸው ሕጎች

፩/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚጋጭ ማንኛውም ሕግ ተፈፃሚነት የለውም።

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የከፍተኛ ትምህርት አዋጁ እና ሌሎች ከከፍተኛ ትምህርት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሕጎች ከዚህ አዋጅ ዓላማ እና ድንጋጌዎች ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ እንደ አግባብነታቸው ተፈፃሚ ይሆናሉ።

2/ The Ministry may issue Directives for the implementation of this Proclamation and Regulations issued pursuant to this Proclamation.

## 46. Transitional Provisions

1/ Upon the reestablishment of an existing university as autonomous, fixed assets of the former university including governmental budget allocated to it before reestablishment, shall be transferred to the new autonomous university.

2/ Where a university is reestablished as autonomous, debts and liabilities owed by the former university shall be transferred to the autonomous university.

3/ The Ministry may decide for a transitional period during which the university functions like any other public university under the Higher Education Proclamation and the university builds its capacity to exercise its academic and institutional autonomy under this Proclamation.

4/ The transition envisaged in Sub-Article (3) of this Article shall not be longer than two years as of the date of the reestablishment.

## 47. Inapplicable Laws

1/ Any law inconsistent with this Proclamation shall not be applicable.

2/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the Higher Education Proclamation and other laws related to higher education shall be applicable, as appropriate, to autonomous universities to the extent they are compatible with this Proclamation and its objectives.

**፵፰. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ሥራ ላይ ይውላል፡፡

**አዲስ አበባ መስከረም ፳፭ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም.**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**48. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force up on the date of its publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, on this 6th day of October, 2023.**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**